# የኮሎኔል አስናቀ እንግዳ ልዩ የክብር ቀን

# በአሲምባ ውይይት መድረክ

ክቡራትና ክቡራን የአሲምባ ውይይት መድረክ ታዳሚዎች ፣ የኮሎኔል አስናቀን ይህን ልዩ የክብር ቀን ምክንያት በማድረግ ጥሪአችንን ተቀብላችሁ ተካፋይ ለመሆን ከመካከላችን የምትገኙ የክብር እንግዶቻችን ፣ እንዲሁም ይህቺን ቀን የምናከብርልዎ የተከበሩ አባታችን ኮሎኔል አስናቀ እንግዳና በማካከላችን የምትገኙ ቤተ ሰቦቻቸው እንኳን ወደ አሲምባ የውይይት መድረክ መጣችሁልን።

ክቡራትና ክቡራን ፤

በሀገራችን የጀግኖች ታሪክ ማስታወሻ ፣ ያውም የቀናቸው ፣ በጣም ጥቂቶቹ ፣ በመቃብራቸው የምትነበብ አንዲት ሉክ መጣጥፍ ማነብነብ የተለምዶ ዘመን አመጣሹ አንካሣ ባሕላችን ገጽታ ነው። ,,,ኢትዮጵያ ሀገሬ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ,,,, እንዲሉ ፣ እንደ ኮሎኔል አስናቀ ያሉ የኢትዮጵያ ኩራት የቁርጥዬ ቀን ጀግኖች ፤ በሀገራችን የመከራ ጊዜ ሁሉ ለወገን አለኝታዎች ፣ ከሁሉ በንቃት ቀድመው የሚሰነዘረውን ጥቃት እንደየአማጣጡ መካቾች ፣ በመሪነትና ፣ በመሥዋዕትነት ከወገናቸው በፊት የመከራን ገፈት ቀማሾች ፤ የድሃ ጠበቆች ፣ እናጅሬ ከተፎዎች ፣ ሀገርን ወዳዶች ፣ ሕዝብን አክባሪዎች ፣ ደሞዛቸው መስዋዕትነት ፣ ክብራቸው ኢትዮጵያዊነት ፣ እንደነአያ የድል አጥቢያ አርበኞች ለሥልጣን ሲሯሯጡ አይታዩም። ተልዕኮአቸውም አይደለምና። ይሄ ሁሉ መልካም ግብራቸው የሚነገር ካለፉ ከብዙ ትውልድ በኋላ ቢሆንም የአሲምባ ውይይት መድረክ እንደነዚህ ያሉ ወገኖች የኢትዮጵያዊነት ጠንካራ መሠረቶች መሆናቸውን ያለጥርጥር ስለሚያምንና ፣ በተለይም አሁን ከመቼውም የበለጠ ኢትዮጲያዊነት እየተቦረቦረ ባለበት ወቅት ፣ በሕይወት ያሉ አሁንም በትግልና በማታገል ላይ ያሉትን እኒህን አባታችንን በዚህ መድረክ አቅርበን ስናመሰግን ፤ እንደሳቸው ሌሎችንም ታሪክ ሰሪ ጀግኖች አይዞአችሁ ፣ በርቱልን ፣ መሪነታችሁ አይለየን ፣ መስዋዕትነትን ለመማር ዝግጁ ነን ብለን ፤ ራስን መጠራጠርንና እስ በሳችን አለምተማመንን ፣ አሽቀንጥረን ጥለን ከያዘን የውድቀት ሰመመን ያባንነናል ብለን ስለምናምን ነው።

የአሲምባ ውይይት መድረክ በዚህ ዓመት የጀመረውን የሀገር ወዳዶች/የጀግኖች ቀን በመቀጠል እነሆ በዛሬው ቀን ይህን ልዩ ዝግጅት የዞላችሁ ቀርቧል።

የዛሬውን ዝግጅት ልዩ የሚያደርገው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጨቋኝ ሥርዓትች ራሱን ለማላቀቅ ባደረጋቸው የትግል ታሪኩ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ሊኖራቸው የሚገባ ፣ ለሀገራችን በአበረከቱትና እያበረከቱ ባለው አስተዋጽዖ ፣ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ባላቸው ፍቅር ፣ በሦሥት ትውልድ ፣በሦሥት የተለያዩ ጨቋኝ ሥርዓቶች ማለትም በዓፄው ዘመነ መንግሥት ፤ በደርግ ጊዜና በዛሬዎቹ የጠባብ ብሔተተኞች መንጋ አስከፊ ሥርዓት ፣ ግንባራቸውን ሳያጥፉ ፣ ደከመኝ ሳይሉ እየታገሉና እያታገሉ ያሉትን እኒህን የምንኮራባቸውን የዕድሜ ባለ ፀጋ ኮሎኔል አስናቀ እንግዳን በሕይወታቸው እያሉ ታሪካቸውን የምንዘክርበት ብቻ ሳይሆን ፣ በዚህ መድረከ የተሰባሰብን ሀገር ወዳዶች በግለሰብ እያንዳዳችን ወጥተን ፣ ለራሳቸው ፣ ለከፈሉት መስዋዕትነት ፣ በተግባር ላሳዩንና እያሳዩን ላሉት አርአያነታቸው ከፍተኛ ምስጋና ለመስጠትና እኛም ፈለጋቸውን ለመከተል ቃል ኪዳን የምንገባበት አጋጣሚ ዕድል የምናገኝበት ጊዜ ስለሆነ ነው።

ክቡራትና ክቡራን ፤

ኮነሌል አስናቀ እንግዳን በዚህ ዝግጅት በዛሬው ዕለት ለማቅረብ ስንነሳ ዋናው እይታችን ለየት ባለ መልኩ ስለ እራሳቸው፡ ስለ አሳለፉት ሕይወታቸው፡ ከልጅነት ዘመናቸው ወደ ውትድርናው፡ ከዚያስ ወዴት? እንዴት ሀገር ለቀው ሊሰደዱ ቻሉ? አሁንስ በዚህ እሰየው በሚያሰኝ በተቸሩት ዕድሜያቸው ጥንካሬን ሰጥቶአቸው ምን እየሠሩ ነው? የሚሉትን ጥያቄውች በቅርብ ከሚያውቋቸው ወገኖችና ቤተ ዘመዶቻቸው እንደበት እንሰማ ዘንድ፡ ይተርኩልን ዘንድ ፈቃደኛ ሆነው ዕድሉን በማግኘታችን እየተደሰትን ይህን አኩሪ ታሪካቸውን  በማስማት ለታሪክ ማህደርነት ይበቃ ዘንድ በማሰብ፡ ወጣቱ ትውልድና ሀገር ወዳዱ ኃይል ከኚህ አባታችን ሊቀሰም የሚገባውን ተመክሮ ግንዛቤ በመስጠት፡ በሕይወት ውጣ ውረዳቸው ያካበቱትን ተመክሮ አካፍለውን ትምህርት መቅሰም ይቻል ዘንድ፡ ምክራቸውን ለማሰማት የበኩላችንን ለማበርከት ነው።

ኮለኔል አስናቀን በአካል የሚያውቋቸው፡ ስለ እሳቸው የሚያውቁትን እንዲያካፍሉን፡ ትዝታቸውን፡ ጥንካሬአቸውን፡ ለሀገርና ሕዝብ ያላቸውን ፍቅር በተለያየ አጋጣሚ አብረዋቸው በቅርብ የሠሩትን፡ የተገናኙትን፡ በሀገር ቤትና በስደት ሕይወታቸው አብረው የኖሩትን፡ የሚያውቁትን ያካፍሉን ዘንድ በመጋበዝ ዋቢ ለማካተት ሞክረናል። ይህ ደግሞ በአንድ በኩል በራሱ በእሳቸው ዕድሜ ባይደርሱም በአዛውንትነት የሚመደቡ አባቶች/እናቶች፡ ምሁራን፡ ሀገር ወዳዶች፡ ታዋቂ ግለሰቦች ከዕድሜ ባለጸጋው አባታችን ምን እንማራለን? ብለው እራሳቸውን እንዲጠይቁ፡ እንዲመረምሩ፡ ቆም ብለው የኋላውንና የፊታቸውን ያስተውሉ ዘንድ ግንዛቤ ይሰጣል ብለን እንገምታለን።  በሌላም በኩል አባታችን በዚህ ዕድሜያቸው ከላይ እታች እየተንቀሳቀሱ አሁንም ሕብረተሰቡን እያገለገሉ መሆናቸው፡ ጽናቱና ጥንካሬው እስካለ በትግሉም መስክ ዕድሜ ወሳኝነት እንደሌለው፡ ብዙዎች ትምህርት እንዲገበዩና እንደ ኮነሌል አስናቀ ዓይነት ጀግና አባት መኖራቸውን ለማያውቁ ደግሞ እንዲያውቋቸው፡ ትልቅ ትምህርት ሊቀሰምባቸው የሚችሉ የሀገር ፍቅርን፡ የሕዝብ ፍቅርን ያስተማሩና እያስተማሩ ያሉ በመሆኑ ትምህርታቸው፡ ተግባራቸው ለሁሉም አርሃያ ይሆን ዘንድ በጥሞና እንድትከታተሉን እንጋብዛለን።

ሀገራችንና ሕዝባችን እስከዛሬ በየጊዜው በተፈራረቁ አምባገነኖች መብቱንና ነፃነቱ ተነፍጎ ፣ ተለጉሞ ፣ ተገርፎና ታሥሮ ብዙዎቻችንን ለስደት የዳረገ ጉዳይ መሆኑ አይካድም። በሀገራችን ምድር ሆነን እንዳንሟገት እንኳ ዕድሉን አላገኘንም። ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደጠላት ተፈርጀን ድንበር ጥሰን እንዳንገባ፡ ከሕዝባችን ጋር የመከራው ገፈት እንደቀመስነው ሁሉ አሁንም መከራውን እየተቋደስን ከሕዝባችን የነፃነት ተጋድሎ ጋር በአካል ተገኝተን መታገሉን ብንናፍቀውም ሳንወድ በግድ ባህር ማዶ እንድንሻገር በሀገር ጠላቶችና በባዕዳን ኃይሎች የተቀነባበረ ሴራ የተሰናከልን በርካታ እንደመሆናችን መጠን ኮነሌል አስናቀ እንግዳ አንዱ የዚሁ ተቋዳሽ ናቸው።

ኮነሌል አስናቀ ኢትዮጵያ ሀገራችን በነፃነት የሕዝቦቿ ሀገር እንድትሆን ታግለዋል፣ አታግለዋል፣ የተቻላቸውን ሁሉ አበርክተዋል። ዛሬም ከዚህ ጉዞአቸው ዕድሜ አላገዳቸውም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሀገሩ ባዳ እንግዳ እንዳይሆን አስተምረዋል። የሀገሩና የመብቱ ባለቤት እንዲሆን ብግል ብዙ መስዋዕትነትን ከፍለዋል። ሀገራችን ሉዑላዊነቷ ተከብሮ፣ ሕዝባችን አንድነቱ ተጥብቆና ተከብሮ እንዲኖር ትልቅ አስተዋጽዖ አድርገዋል። እያደረጉም ይገኛሉ። ይህ ምኞታቸው ተሳክቶ፣ ሀገራችንና ሕዝባችን ከወያኔና ጠባብ አምባገነን ገዥዎች ለአንዴም ለመጨረሻ ተላቃ ፣ የእውነተኛ ሕዝባዊ ሥርዓት መሠረት ተጥሎ ለማየት ያብቃቸው እያልን፣ በክብር፣ በደስታ፣ በዕልልታ፣ በነፃነት ወደ ሀገራቸው ምድር ገብተው አረንጓዴ-በጫ-ቀይ ሰንደቃችንን ከፍ አርገው አውለብልበው፣ ዝቅ ብለን ተቀብለናቸው፣ አደራውን ለመረከብ ሁላችንንም ያብቃን እያልን ከፍተኛ ምኞታችንን በአሲምባ የውይይት መድረክ ስምና በታዳሚዎቻችን እንዲሁም በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም እንገልጽላቸዋለን። እንመኝላቸዋለን።

ያለጥርጥር ኢያትዮጵያዊነት ያቸንፋል!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

የአሲምባ ውይይት መድረክ

ነሐሴ 10 ቀን 1999 ዓ.ም.
(ኦውገስት 18, 2007)